# ይድረስ ለወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ

**(ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች)**

Click hear for Audio

ወ/ሪት ብርቱካን ይህን መልዕክት ያስተላለፉልኝ እነማን ናቸው ብለሽ ግር እንዳይልሽ ጥቂት ስለኛ ለማለት ወደድን፡፡ እኛ የኢትዮጵያ ፍቅር አንገብግቦን፣ የሕዝባችን ረሃብና ጥም አሳዝኖን፣ የወገናችን የዴሞክራሲና የፍትሕ እጦት አቃጥሎን ወደ ትግል የገባን ኢትዮጵያውያን ወጣት ተማሪዎች ነን፡፡ ወደ ትግል የገባነውም ቅንጅትን ከመሠረቱት አራት ፓርቲዎች አንዱ በሆነው በቀስተዳመና ፓርቲ በኩል መሆኑንም በዚህ የጽሁፋችን መግቢያ መግለጽ እንሻለን፡፡

ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘ በተፈጠረ ችግር ድምጻችን መሠረቁን የተቃወሙ ወገኖቻችን ሲገደሉ፣ የፓርቲ መሪዎቻችንና በርካታ ዜጎቻችን ሲታሰሩ፣ ሌሎች ከአገር ሲሰደዱ፣ ከቤት ንብረታቸውና ከሥራቸው ሲፈናቀሉ ልባችን እጅግ አድርጎ አለቀሰ፡፡

እናም በወቅቱ ከግድያና ከእስር የተረፍን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የተዳፈነውን ትግል ለማፋፋም የበኩላችንን ድርሻ ለመወጣት ቁርጠኛ ውሳኔ አደረግን፡፡ በዚህም መሪዎቻችን ከእስር እንዲፈቱ ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጥር 19 ቀን 1999 ዓ.ም በጻፍነው ደብዳቤ ጠየቅን፡፡

ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀጥለንም በዚሁ ወር ለአፍሪካ ኅብረት ዋና ፀሐፊ ተመሳሳይ አቤቱታ አቀረብን፡፡ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የላክነውን ደብዳቤ ኮፒም የካቲት 3 ቀን 1999 ዓ.ም በአዲስ አድማስ ጋዜጣ በቁጥር 367 በቅጽ 8 ላይ እንዲወጣ አደረግን፡፡ በተከታታይም ለአሜሪካ፣ ለሲውዲን፣ ለናይጄሪያ፣ ለኖርዌይ፣ ለካናዳ፣ ለእንግሊዝ፣ ለኡጋንዳ፣ ለደቡብ አፍሪካ እና ለሌሎችም ኤምባሲዎች እንዲሁም ለተወካይ ምክር ቤት አቤቱታችንን አሰምተናል፡፡

በጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብና በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ትግል መሪዎቻችን ሲፈቱልን በጣም ተደሰትን፡፡ ነገር ግን ወ/ሪት ብርቱካንና መሰሎችሽ ያልጠበቅነው አካሄድ በማድረጋችሁ ይህን ጽሑፍ ለመጻፍ ተገደድን፡፡

- ✷ በጽሑፋችን ውስጥ ባስቀመጥነው ሃሳብ ሁሉ ‹‹አንቱ›› ወይም ‹‹እርሶ›› የሚሉ አባባሎችን አልተጠቀምንም፡፡ ምክንያቱም ከምርጫ 97 በፊት ጀምሮ በቀስተዳመና በኩል በአባልነት ስንቀሳቀስ አንቺን ለመጥራት አብዛኞቻችን እነዚህን አባባሎች ተጠቅመን ባለማወቃችንና፤ አንቺንም የቅርባችን ለማድረግ ካለን ፍላጎት የተነሳ ነው፡፡ ዛሬም እንደድሮው አጠራራችን ልንጠቀም ወደናል፡፡ ችግር ኖሮት ቢገኝ እንኳን አስቀድመን ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡

EthioLion.com

- ወ/ሪት ብርቱካን አብዛኞቻችን በቀስተዳመና በኩል ቅንጅትን ከተቀላቀልንበት ጊዜ አንስቶ ማለትም ከ97 ምርጫ ጥቂት ወራቶች በፊት መሆኑ ነው፤ ከእስር እስከተፈታችሁበት ጊዜ ድረስ ለሁላችሁም የቅንጅት አመራሮች እጅግ ጥሩ የሆነ አመለካከት ነበረን፡፡ በተለይ ደግሞ በከፍተኛ አመራር ቦታ ላይ ለነበራችሁት፡፡ ዛሬ ወደ ኋላ ተመልሰን ከምርጫ በፊት እና በኋላ የነበራችሁበትን ሁኔታ መተረክ አይጠበቅብንም፡፡ ምክንያቱም ከእስር ከተፈታችሁ በኋላ አዲስ እና አስደንጋጭ የመከፋፈል ስሜት ይዛችሁ ብቅ ስላላችሁ፡፡ ውስብስብ ሆኖ ባላው በቅንጅት ችግር ላይ ለማተኮር እንገደዳለን፡፡
- ወ/ሪት ብርቱካን በዚህ ጽሑፍ የምንገልፅልሽ በአንድ ጀንበር የመጣ ሳይሆን ከእስር ተፈታችሁ ወደ ውጩ አገር ከሄዳችሁበት ጊዜ አንስቶ ሰባት ወራቶችን በችግሩ ላይ ስናጠና ከቆየን በኋላ የደረስንበትን አቋም ነው፡፡ በዚህ ብቻ ሳናበቃ በስተመጨረሻ በክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ከሚመራው ቅንጅት ቢሮ ጋር በወከልናቸው ተማሪዎች አማካይነት በጉዳዩ ላይ ፊት ለፊት በመነጋገር፤ እንዲሁም ከአንቺው ከራስሽ ጋር በቢሮሽ በወከልናቸው ተማሪዎች አማካይነት በጉዳዩ ላይ ከተነጋገርንበት በኋላ የያዝነው የመጨረሻው አቋማችን መሆኑን ልንገልፅልሽ እንወዳለን፡፡
- ወ/ሪት ብርቱካን ከቅንጅት አመራሮች ጋር ያሳለፍሽው የመከራ ጊዜ መቼም ቢሆን የምንረሳው ባይሆንም፤ አሁን ላይ ግን የያዝሽውን መሰሪ የሆነ ተንኮልና፣ የማፈራረስ አካሄድሽን ስንመለከት ልንታገስሽ የምንችልበትን አቅም አጥተናል፡፡ እያደረግሽው ካለው አፍራሽ እንቅስቃሴ ከነቡድንሽ እንድትታቀቢ እናሳስብሽ ዘንድ ለዴሞክራሲና ለፍትሕ በየሜዳው የፈሰሰው የወንድሞቻችን እና የእህቶቻችን ደም ያስገድደናል፡፡
- እስከአሁን ዝም ብለን እውነት የት ጋር እንዳለ ለማጣራት የእያንዳንዳችሁን እንቅስቃሴና ንግግር ስንከታተል ብዙ ወራቶችን ካሳለፍን በኋላ፤ ዛሬ የጠራና የነጠረ እውነታ ላይ ስለደረስን ከዚህ በኋላ መደናገሩም ሆነ ማደናገሩ የሚያዋጣ ስለማይሆን ቢበቃሽ ጥሩ ነው ለማለት ተገደናል፡፡
- ወ/ሪት ብርቱካን ለመሆኑ ምን ዓይነት የጎሊና መታወር ቢገጥምሽና፤ የሕዝብ ንቀት ቢሞላሽ ይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ፓርቱን «ቅንጅትን» በማፈራረስ ተግባር ላይ የተሰማራሽው? ወደ ሰሜን አሜሪካ የሄዳችሁበትን የማስታረቅና የማስማማት ሥራ ወደ ጐን በመተው በድጋፍ ሰጪ ማኅበራት መካከል የተፈጠረውን ችግር ከማርገብ ይልቅ በማራገብ ማቀጣጠላችሁ በእጅጉ አሳዝኖናል፤ አሳፍሮናልም፡፡ ይባስ ብላችሁ «የአፍራሽ ግብረ ኃይል ስብስብ» ብለን ከሰየምናቸው ከቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር አባላት (KIL) ጋር በተጣመረ መልኩ እነሱን በማጠናከር ለመሥራት ያቀዳችሁትን

ቅንጅትን የመከፋፈል ሴራ ስንደርስበት፤ ቢሳካላችሁ ኖሮ ልታደርሱ የምትችሉትን ጥፋት ስንገምት በጣም አስቆጥቶናል፡፡

- ወ/ሪት ብርቱካን እስኪ አንድ ጥያቄ እንጠይቅሽ የKIL አመራሮች እነማን ናቸው? እነዚያ የሐሰት ፕሮፓጋንዳ ሲዘሩ የነበሩት፤ ገንዘብ ተጭበረበረ ሲሉ የከረሙት አይደሉምን? አሁን በቅርብ ደግሞ የትጥቅ ትግል ነው የሚያዋጣን ሲሉ የሚደመጡት አይደሉምን?፡፡ ከአሁን በኋላ ልንሰማቸው ብቻ ሳይሆን ልናስባቸው የማንፈልጋቸው፤ በንፁህን ደም መፍሰስ የሚስቁ፤ ራሳቸውን አደልበው በሕዝብ እንባ የሚሳለቁ፤ ተኩላዎች መሆናቸውን ግልፅ ልናረግልሽ እንወዳለን፡፡
- ክፍፍል ከመፍጠራችሁ ባሻገር በከፍተኛ ሕመም ላይ የነበሩትን ክቡር ፕሬዚዳንት ኢንጅነር ኃይሉ ሻውልን ትታችሁ ለመሄድ ያደረጋችሁት እሩጫ በጣም ያስገርም ነበር፡፡ ስንቶቻችን ንግግራችሁን ናፍቀን ከእናንተ የሚወጡ መልዕክቶችን ለመስማት በጣም ጓጉተን ነበር? የኋላ ኋላ ግን የውንጀላ፣ የማጥላላትና፣ ክብርን የሚነካ «እድሜን» በመጥቀስ እና በገንዘብ ማጭበርበር ክስ በፕሬዚዳንቱ ላይ ክፉኛ ስትነዙ በመደናገጥ ቆም ብለን ለመመርመር ተገደድን፤ ሆኖም ግን ይህ ውንጀላና ክስ በተጠናከረ መልኩ ሲቀጥል «ምን የተደበቀ ምስጢር ቢኖር ነው?» ብለን ባደረግነው የረጅም ጊዜ ጥናት ቀድሞ የታሰበበትና ክቡር ፕሬዚዳንት ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ላይ ብቻ ሳይሆን ዒላማው የሕዝብ በሆነው ቅንጅትም ላይ ያነጣጠረ መሆኑ ዘግይቶም ቢሆን ገባን፡፡ ብርቱካን ጥቅምሽ ምን ይሆን? የዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ውለታ ለመክፈል? የኢሕአዴግን ይሁንታ ለማግኘት? ወይስ የነጮችን ዳረጎት ለመቋደስ? ሊገባን አልቻለም በእውነት ያሳፍራል፡፡ በተለያዩ ጊዜያት ከኢትዮጵያ ውጪም ሆነ ወደ ኢትዮጵያ ከመጣሽ በኋላ እያራመድሽው ያለ የተሳሳተ አካሄድሽን አሁንም እያራመድሽ መሆንሽን የሚያመለክቱን ነገሮች ብዙ ቢሆኑም በጥቂቱ መጥቀስ ይቻላል፡፡
    - ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሳችሁ በኋላ አንድም ቀን ወደ ቅንጅት ቢሮ ሄዳችሁ የሠራችሁትን ሪፖርት ከማድረግም ሆነ፤ እየተሰራ ያለውን ሥራ ከመጠየቅና ምን እንደደረሰ ከማወቅ ይልቅ በግለሰቦች ቤትና ውጪ ውጪውን ስትሉ ቆይታችሁ ፕሬዚዳንቱ አሜሪካ በሰራችሁት ጥፋት የፈጸማችሁት ነገር ተጣርቶ በገለለተኛ አጣሪ ኰሚቴ ታይቶ ውሳኔ እስኪሰጥ ድንገት እቀባ ሲጥሉባችሁ፤ አይታችሁት የማታውቁት ቢሮ ላይ መጥታችሁ እንግባ አንግባ እያላችሁ የሠራችሁት ድራማ አይሉት ቲያትር በጣም እንድናፍርባችሁ አስገድዶናል፡፡ ይህንንም በቅርበት ከነበሩ ሁኔታውን ከተከታተሉ ግለሰቦች ለመረዳት ችለናል፡፡ ታዲያ ለዚህ ለዚህማ ቲያትር ቤቶች ሞልተውላችሁ

አልነበረምን? የኢትዮጵ ሕዝብ ከእናንተ ድራማ የሚጠብቅ እንዳልሆነ ጠንቅቆ ያውቃል:: ባይሆን ለአቶ ደበበ እሸቱ ብትለቁለት ይሻል ነበር::

- ➡ በተጨማሪ ሌላው እየተገበራችሁት ያላችሁት ደንብና ሥርዓትን ያልጠበቀ የፓርቲ ማቋቋም ሁኔታ እና የጉደሉ የላዕላይ ምክር ቤት አባላትን የማሟላት እንዲሁም አዲስ የፓርቲ ስም የማውጣት እንቅስቃሴ፤ ሕዝብ አደራ ከሰጠው ከአንድ ፓርቲ መሪ የማይጠበቅ ሲሆን ለእኛ ማን ምን እንደሆነና፣ እውነታውን ለማግኘት አመላካች ሆኖናል::
- በቅንጅት መተዳደሪያ ደንብ ላይ የፓርቲ ስምን ሆነ ሌሎች ነገሮችንም ሁሉ የመወሰን ሥልጣን ያለው ጠቅላላ ጉባኤ በሆነበት ሁኔታ አዲስ ፓርቲ ለዛውም «ቅንጅትን የሚተካ ፓርቲ ነው የፈጠርነው...» ማለትሽ አሳፍሮናል:: ጠንቅቀሽ ቅንጅትን የምታውቂው ይመስለናል:: ጠቅላላ ጉባኤ ያለው፣ የላዕላይ ምክር ቤት ወዘተ ያለው ጠንካራ ፓርቲ ሆኖ ሳለ ኢ-ዴሞክራሲያዊ አካሄዳችሁ ገሀድ የወጣበት እንቅስቃሴ ላይ እንደሆናችሁ አይተንበታል::
- የላዕላይ ምክር ቤት አባላትን ለማሟላት ብላችሁ የተከተላችሁት የሕፃን ጨዋታ እራሳችሁን ጠለፋችሁ:: ማንንም ከየመንገዱ አምጥቶ የላዕላይ ምክር ቤት አባል የሚያደርግ መመሪያና ደንብ ቅንጅት የለውም::
- አመራረጡም ተለዋጭ አባላትን መሠረት በማድረግ የተጓደሉ አባላትን የመተካቱ ሂደት ይከናወናል ይላል የመተዳደሪያ ደንቡ:: ታዲያ እነ አቶ ተመስገን የየትኛው ላዕላይ ምክር ቤት ተለዋጭ አባል ሆነው ነው? የትኛውስ ድምፅ ኖሯቸው ነው? በጉደሉት አባላት ተተኩ የምትሉት? ሌሎቹስ ቢሆኑ:: ወ/ሪት ብርቱካን ለዴሞክራሲና ለፍትሕ የምትታገሉበት የሞራል ብቃት ስለሌላችሁ አርፋችሁ ብትቀመጡ ያምርባችኋል:: በተለይ ብርቱካን ምንም እንኳን ታናናሾችሽ ብንሆንም እንምከርሽ፤ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ክፉኛ ከምታበላሺና የሕዝብን የትግል መንፈስ ከምትገድይ፣ ዳግመኛ ልደቱ በመሆን በሞቱት ወገኖቻችን ደም ከመሳለቅ እና በተጐዱ ወገኖቻችን ቁስል እንጨት ከመስደድ እባክሽ አርፈሽ ቁጭ በይ:: **«ማንም የቆመ ቢመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ....» ይላልና ቃሉ::**

**«የወጣችው የነፃነት ፀሐይ ተመልሳ አትጠልቅም» ባልሽበት አንደበት ዛሬ ብዙዎች ውድ የሆነ የሕይወት መስዋዕትነት የከፈሉበትን የነፃነት ጮራ ለማጨለም በቀዳሚነት የምትሯሯጪው አንቺው መሆንሽ አስቆጥቶናል::**

ወ/ሪት ብርቱካን ሁላችንም እንቅስቃሴዎቻችሁን በጥሞና መከታተላችን ለዚህ አቋም እንድንደርስ ቢረዳንም በተጨማሪ ደግሞ በወከልናቸው ተማሪዎች አማካኝነት ላቀረብንልሽ ጥያቄዎች የሰጠሽን መልስ ይበልጥ አቋማችን የፀና እንዲሆን ረድቶናል::

EthioLion.com

ከብዙ በጥቂቱ:-

- ስለ አሜሪካው ጉዞአችሁ ለቀረበልሽ ጥያቄ «.... ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ወደ ውጭ አገር ቶሎ እንዲሔድ ያስቸኩሉን ስለነበር ነው..........» ማለትሽ ምን ያህል የማይታመን ሃሳብ እያቀረብሽ እንዳለ አሳይቶናል::
- ተያይዞ ለቀረበልሽ ጥያቄ በአሜሪካ ቀድማችሁ ስለገባችሁ ለምን ዘግይተው የመጡትን ክቡር ፕሬዚዳንቱን አልተቀበላችኋቸውም?
  - «......እኛ በገባን በጥቂት ቀን ውስጥ ስለመጡ የመቀበሉን ነገር ብዙም ያሰብንበት ነገር አልነበረም....» በመቀጠልም
  - «.....ይህ የመቀበል ነገር እኮ ጠ/ሚኒስትር መለስ ወደ አንድ አገር ሲሄድ አምባሳደሮችና ሌሎች ሰዎች የሚያደርጉት አይነት አቀባበል ስለሆነ ያን ያህል የሚጠበቅብንም ነገር አልነበረም........ያ የአገር ነው ይህ ደግሞ የቅንጅት ነው...» አያይዘሽም
  - «.......በእርግጥ እሳቸውን በመቀበሉና ባለመቀበሉ ሁኔታ ላይ አብረውኝ ለነበሩ ሰዎች እኔ በግሌ እንኳን ሁሉንም ወክዬ ሄጄ እንድንቀበላቸው ሃሳብ አንስቼ ነበር ግን ሁሉም "አርፈሽ ቁጭ በይ ይሄማ Leader Ship ዓይነት ነገር ሆነ እኛ እንደዚህ ዓይነት ነገር የለንም ሲሉኝ ቀረሁ እንጂ ጥያቄውን እንኳን አንስቼ ነበር.....» ብለሽ እርስ በርሳቸው ሊታረቁ የማይችሉ ሦስት መልሶችን ስትደረድሪ ሁላችንም ወጥ ያልሆነ አቋም የሌላችሁና ከባድ የሆነ ንቀት በፕሬዚዳንቱ ላይ እንዳላችሁ አመላክቶናል::
- በቅንጅት ስም ስለታሰሩ እስረኞች፣ በቀረበልሽ ጥያቄ ደግሞ «.......ክሪስ ስሚዝ ሲጠይቁኝ 100 ገደማ ብዬ ነበር አሁን ደግሞ 40 ገደማ ናቸው በቅርቡ ከሽማግሌዎች ጋር ሆነን 26 እስረኞች አስፈትተናል.....እና ባለኝ በአዲስ አበባ መረጃ ይህን ይመስላል.....»
- በምርጫ 97 ምክንያት የታሰሩት በየሰፈራችን የምናውቃቸው እናንተ በአመራር ቦታ ያላችሁትና ሽማግሌዎቹ የማታውቋቸው እስረኞች ቅንጅት አይመለከተውም ማለት ነው? ማነው ለነሱ ሊቆም የሚችለው? ስንልሽ

«...እንደሱማ አትበል....ይመለከተናል እንጂ.... ይህን ያህል ብዙ እስረኛ ግን ይኖራል ብዬ አላስብም አልኩህ እኮ 40 እስረኞች በአዲስ አበባ ውስጥ አሉ»

በገጠር የታሰሩትስ ቅንጅትን አይወክሉም ማለት ነው?

«.... በእርግጥ የገጠሩ አካባቢ መረጃ የለኝም... ግን በደዴሳ ምንም እስረኛ እንደሌለና በዝዋይ 3 (ሦስት) ብቻ እስረኞች እንዳሉ አውቃለሁ...» ወ/ሪት ብርቱካን መረጃ ሳይኖርሽ የአዲስ አበባና የገጠር እያልሽ እንዴት በአሜሪካን ኮንግረስ ፊት

ምስክርነትሽን ልትሰጪ ቻልሽ? ማደናገር ይሆን መደናገር? ነው ወይስ ይህን ሕዝብ የመስዋዕት በግ አርገሽ ከኢሕአዴግ ልትታረቂበት ይሆን?

- ከነ አቶ ልደቱ፣ ከአየለ ጫሚሶ ጋር እንዲሁም ከሌሎች የፓርቲ መሪዎች ጋር እንዴት አብሮ ለመሥራት በቅንጅት ስም ሞከርሽ? ይህን የሚጠቁሙ መረጃዎች አሉን። ባልንሽ ወቅት

  **«.... በእርግጥ ከልደቱ ጋር አንዴ መንገድ ላይ ተገናኝተናል ለሁለተኛ ጊዜ ደግሞ የፈረንሳይ ኤምባሲ ግብዣ አድርጎልን ተገናኝተናል። እንግዲህ በሰሜን አሜሪካ ደግሞ እኛ እዛ እያለን ልደቱ ብቻ ሳይሆን አቶ አየለ ጫሚሶ፣ ዶ/ር መረራ ጉዲና፣ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፣ ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ የተገናኘንበት ሁኔታ ተፈጥሯል በዛ ወቅት የኢሕአዴግ ሰዎችም ነበሩ....ይሄን ያህል የሚያስብል የተዋዋልነው ውል የለም............» አልሽን።**

ወ/ሪት ብርቱካን አቶ ልደቱ የፈፀመው የሕዝብ ክህደት ለአንቺ የተደበቀ ሆኖ ነውን? አቶ አየለ ጫሚሶ የኢሕአዴግ ታማኝ መሆናቸው ካንቺ ተሰውሮ ነውን? በግልፅ «አመፀኞች፤ ሁከተኞች» ሲል የነበረ ግለሰብ፤ ሕዝቡንና በእስር የነበረውን የቅንጅት አመራር ነውጠኞች ሲል የከረመ ሰው አይደለምን? ታዲያ ምን ተዓምር ተፈጥሮ ነው ከሄዳችሁበት የቅንጅት ተልዕኮ ውጪ፤ ለዛውም ክቡር ፕሬዚዳንቱ ባሉበት ምድር እንደዚህ ዓይነት የተቀነባበረ ሸፍጥ የሰራችሁት ያውም ከአቶ ልደቱ፣ ከአቶ አየለ ጫሚሶ ጋር።

- **የቡድንሽ አባላት የሆኑት ኢንጅነር ግዛቸውና አቶ ብሩክ ከበደ HR2003 ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደማያስፈልገው የነገሩን በእውነት በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት መከበር አሁን ላይ አያሳስበንም ብላችሁ ተስማምታችሁ ይሆን? በጣም ተሳስታችኋል በቡድናችሁ ሥራ እጅግ በጣም አፍረናል።**

- ወ/ሪት ብርቱካን ......ቅንጅት ስላደረጋቸው የፈጠራ በደል የትግራይን ሕዝብ ይቅርታ ስለመጠየቅሽ ስንሰማ የትግራይን ሕዝብ ከቅንጅት የትግል ጐራ የማግለል ክፉ የሆነ አሳብሽን አጥብቀን ተቃወምን። «ቅንጅት የትግራይን ሕዝብ በደለ» ስትይ ቅንጅት የሕዝብ እንደሆነ አጥተሽው ነው? ወይስ የትግራይ ሕዝብ እራሱ የቅንጅት አካል መሆኑን ዘንግተሽ? ቅንጅትንና የትግራይን ሕዝብ ለመለየት ያደረግሽው አፍራሽ እንቅስቃሴ ኢሕአዴግ የቅንጅትን አመራሮች በእስር ቤት የከሰሰበት 1ኛው የዘር ማጥፋት ወንጀል ነበር። ፍርድ ቤቱም ይህንን በዘር ማጥፋት ላይ አነጣጠረ

የተባለውን ክስ ውድቅ እንዳረገው ይህም ጉዳይ በቅንጅት አመራሮች እንቅስቃሴ ላይ እንዳልታየ የወሰነውን ውሳኔ ታውቂያለሽ:: ዛሬ አንቺ ተመልሰሽ ቅንጅትን መክሰስሽ የጨለምተኝነት ጉዞ ላይ እንዳለሽ ያመላክታል::

- በስተመጨረሻም ከላይ የጠቀስናቸው ከብዙ በጥቂቱ በትክክል ያለንን አቋም የሚያንፀባርቁ ሲሆኑ ጐን ለጐን ስንከታተለው የነበረውን **በኢንጅነር ኃይሉ ሻውል የሚመራውን ቅንጅትን በመደገፍ ከአሁን በኋላ ከቅንጅት ቤተሰቦች ጋር በመቀላቀል እንደቀድሞው በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ወስነናል::**
- በዚሁ አጋጣሚ ባደረግነው የረጅም ወራት እውነታን የመፈለግ ሂደት ውስጥ ከወ/ሪት ብርቱካን እንቅስቃሴ ይልቅ በገንቢነቱና፣ ሕዝብን በማረጋጋቱ ዙሪያ ከፍተኛ የሆነ ሚና የተጫወተውን በክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል የሚመራውን ቅንጅትን ከልብ እናደንቃለን:: ከጐናቸው ለመሰለፍና በምንችለው ሁሉ ለመንቀሳቀስ መወሰናችን ግልፅ ለማድረግ እንፈልጋለን::
- የደረስንበትን እውነት ባለንበት ማኅበረሰብ ውስጥ ግልፅ ለማድረግ፣ የበኩላችንን ለማበርከትና ቅንጅትን ለመገንባት በሚደረገው ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ በቁርጠኝነት ተነስተናል::

***እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!***
***ቅንጅት አንድ ነው!***
***ኢትዮጵያም አንድ ናት!***

**የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች**
**አዲስ አበባ**
**መጋቢት 10/2000 ዓ.ም**